# የኢትዮጵያ የይርጋ ሕጎች መሰረታዊ ሀሳቦች

በወርቅነህ አለምነው*

## 1. መግቢያ

የይርጋ ጽንሰ ሀሳብ የሚመነጨው "ረጋ" ከሚለው የአማርኛ ቃል ሲሆን "ረጋ" የሚለውን ቃል ደራሲ ተሠማ ኃብተ ሚካኤል "የሰው ሀሳቡ ከመውጣት ከመውረድ በሀሳብ ከመዞር ከመባከን ከመናወጥ ፀጥ አለ" በሚል ገልጸውታል፡፡[1] ከዚህ በመነሳትም ይርጋ የሚለው ቃል የአንድ ሰው የመብት ጥያቄ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ቀሪ የሚሆንበትና ባለ እዳውም ከሚቀርብበት ክስ ስጋት እፎይ የሚያስብል የህግ መርህ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡[2] የህግ ምሁራን እንደሚገልጹት ሁለት አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አይነት የይርጋ ደንብ ያልነበረ መብት የሚያስገኝ (acquisitive prescription) በመባል የሚታወቅ ሲሆን አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን አግባብ የሚፈጥር የይርጋ ደንብ ነው፡፡[3] ሁለተኛው አይነት የይርጋ ደንብ ደግሞ ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ (liberative prescription) የሚባል ሲሆን ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው፡፡[4] ይህ ጽሁፍ በማህበረሰባችን ውስጥ ሁለቱም የይርጋ ደንብ አይነቶች በተደጋጋሚ ለክርክር ምክንያት እየሆኑ በመሆኑ የሁለቱም የይርጋ ደንብ አይነቶች መሰረታዊ ባህሪወችን አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ የህግ ድንጋጌወች እና የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት(ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠ/ፍ/ቤት) ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው የይርጋ ህግ ትርጉሞች ጋር በማገናዘብ ይመረምራል፡፡

ይርጋን በተመለከተ ሁሉም አይነት የኢትዮጵያ ህጎች ተመሳሳይ የይርጋ ጊዜ የሌላቸው በመሆኑ ለእያንዳንዱ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ ወይም ያልነበረ መብት ለማግኘት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ፣ የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምርበት ጊዜ፡ በሕግ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ

* LL.B, በንግድ ህግ LL.M፣ ቀደም ሲል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ በአሁኑ ጊዜ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህር፣ ማንኛውንም አይነት አስተያት በ ኢ-ሜ-ል አድራሻ worknehalemnew@gmail.com መላክ ይችላሉ፡፡ ለዚህ ጽሁፍ መሳካት ገንቢ አስተያየቱን ለሰጠኝ አሰልጣኝና ተመራማሪ አቶ ጋሻየ ቢያድጌ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

[1] ተሰማ ሀብተ ሚካኤል "ከሡቴ ብርሀን ተሰማ" የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፣ ኩራዝ አሳታሚ፣1972 ዓ.ም፣ ገጽ 280

[2] Garner Black, Blacks law Dictionary, 9th Edition, 2004, West Publishing Company, p. 723.

[3] ዝኒ ከማሁ፣ እንዲሁም George Krzeczunowicz, Formation and Effect of Contracts in Ethiopian Law, Faculty of law, Addis Ababa University, 1983, page 181.

[4] ጥላሁን ተሾመ፣ የውል ህግ መሰረታዊ ሀሳቦች፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ፣ 1999 ዓ.ም ገጽ 181

ሊቋርጥ የሚችልባቸው ምክንያቶች እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች በዚህ ጽሁፍ ተካተዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጽሁፍ የይርጋ ደንቦች መሰረታዊ ሀሳቦች፣ አላማወች፣ ስለሚያስጠብቋቸውና ስለሚፈጥሯቸው መብቶች እንዲሁም የይርጋ ደንብን የተመለከቱ የተለያዩ የኢትዮጵያ የህግ ድንጋጌወች ይመለከታል፡፡ በዋናነት ግን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ድንጋጌወችን አስመልክቶ በፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፤ በውል ህግ፣ በውርስ ህግ፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ፣ ከውል ውጭ ሀላፊነት፣ በንግድ ህግ፣ በቤተሰብ ህግ፣ በንብረት ህግ እና በወንጀል ህግ ላይ የሰጣቸውን 70 (ሰባ) የህግ ትርጉሞች በመዳሰስ የኢትዮጵያ ይርጋ ህጎች መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የአንባብያንን ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ ጽሁፍ ነው፡፡

# 2. የይርጋ ሕግ ዓላማ

## 2.1. ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ (Acquisitive Prescription) አላማ

የይርጋ ደንብ የራሱ የፖሊሲ መሰረት ያለው ነው፡፡ የንብረት ባለቤትነት አጀማመር ከይዞታ መብት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳለው በመስኩ ምርምር ያደረጉ የህግ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡[5] የሰው ልጅ ለህልውናው አስፈላጊ የሆኑ ጠቃሚ ንብረቶችን በይዞታው ስር ማዋል ሲጀምር የግል ንብረት (private property) ጽንሰ ሀሳብ ተከሰተ፡፡ ባለቤቱ የለቀቀውን ወይም ባለቤት ያልነበረውን ንብረት አስቀድሞ የያዘ ሰው በንብረቱ ላይ ከሌሎች ሰወች የተሻለ መብት እንዳለው ህብረተሰቡ እውቅና ሲሠጠው የይዞታ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ባለቤትነት (ባለሀብትነት) ጽንሰ ሀሳብ ተለወጠ፡፡[6] ከቀደምት ብሂሎች መካከል "አስቀድሞ በእጅ ማድረግ የማይገሰስ መብት ነው" (the devine right of grab) የሚለው ብሂል የረጅም ዘመን ይዞታን ወደ ባለቤትነት የሚለውጠውን ያልነበረ መብት ለሚያስገኘው የይርጋ ደንብ መነሻ እንደሆነ የህግ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡[7]

ስለሆነም ያልነበረ መብት የሚያስገኘው የይርጋ ደንብ አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን እድል ይፈጥራል፡፡[8] የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ቀድሞ ከእርሱ የተሻለ መብት የነበረው ሰው ቢመጣም የቀድሞ ባለሀብቱ ነበርኩ ብሎ መብቱን ሊጠይቀው አይችልም፡፡ በንብረቱ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት ለቆየው ሰው ያለፈው ጊዜ ከንብረቱ

---

[5] G. Paton, Philisophy of law, West Publishing Company, 1945, page 485-489
[6] ጥላሁን ተሾመ፣ የግርጌ ማስታወሻ 4፣ ገጽ 182
[7] ዝኒ ከማሁ
[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 181

ካገኘው ቁሳዊ የሆነ ጥቅም ባሻገር የባለቤትነት ስሜትንም ለመፍጠር በቂ እንደሆነ ህጉ ይገምታል፡፡ የዚህ ይርጋ ደንብ ዋና አላማም በንብረት ባለቤትነት ላይ ሰላምንና መረጋጋትን ማረጋገጥ ነው፡፡[9] የህግ ፍልስፍና ሊቅ የሆኑት ጆርጅ ፓተን እንደገለጹት አንድ የመብት ጥያቄ በህግ ፊት ተቀባይነት ቢኖረውም እንኳን ሊቀርብ በሚችልበት ጊዜ ላይ ገደብ ማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡[10]ህጉ ዳተኛውን ባለገንዘብም ቢሆን ማስጠንቀቅ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም የይርጋ ደንብ የሚፈጥረው አጠቃላይ ዋስትና ከጉዳቱ አንጻር ሲታይ ሚዛን ይደፋል፡፡

## 2.2. የግዴታ አስቀሪ ይርጋ ደንብ (Liberative Prescription) አላማ

ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ (liberative prescription) ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው፡፡ ስለሆነም ባለገንዘቡ በባለእዳው ላይ ክስ የማቅረብ መብቱን ሳይጠቀምበት በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ክስ የማቅረብ መብቱን ያጣል፡፡ የዚህ ይርጋ ደንብ አላማም በዋናነት ተከሣሽን ብዙ ጊዜ ካለፈው ክስ ለመጠበቅ ሲሆን ለዚህም ሦስት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡[11] የመጀመሪያው ህጉ የሚያግዘው ቀልጣፋን ባለመብት እንጅ ዳተኛውን ባለመብት ባለመሆኑ ከሣሽ በቅን ልቦና መብቱን ለማስከበር ከፈለገ ጉዳዩን በተቻለው ፍጥነት ማቅረብ ይኖርበታል ከሚል ሀሣብ የተነሳ ነው፡፡[12] ሁለተኛው ምክንያት ጉዳዩ ከመዘግየቱ የተነሣ ተከሣሽ ክሱን ለማስተባበልና ለመከላከል ማስረጃዎችን ሊያጣ ይችላል የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ እጅግ ዘግይተው የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎች ፍትህ ከማስገኘት ይልቅ በክፉ ልቦና ተከሳሹን ለማጥቂያ መሳሪያነት ስለሚውሉ ይህንኑ ለመከላከል ስለመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በተፃፉ በርካታ ፅሁፎች ላይ ተመልክቷል፡፡[13] ስለዚህ የእውነት መብቱን ማስከበር የፈለገ ሰው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ክሱን መመስረት ይኖርበታል፡፡ በጣም ዘግይቶ ከመጣ ግን በመዘግየቱ የተነሣ የራሱን መብት ከማስከበር ይልቅ በተከሳሹ ላይ አላስፈላጊ ጫና ስለሚያሳድር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡[14]

---

[9] Daniel W.Ambaye, Applicability of period of limitation in rural land dispute: case comment, Bahirdar University Journal of Law, volume 5, Number 1, 2014፣ page 225.
[10] G. Paton, Philisophy of law, West Publishing Company , 1945, page 485-489
[11] Halsbury's Law of England, 4th edition, as cited in Daniel W.Ambaye, Applicability of period of limitation in rural land dispute: case comment, Bahirdar University Journal of Law, volume 5, Number 1, 2014፣ page 225.
[12] Halsbury's Laws of England, 4th edition, በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 225 እንደተጠቀሰው
[13] ዝኒ ከማሁ
[14] Rene David, Commentary on Contracts in Ethiopia, translated by Michael Kindred, 1973, Haile Sellassie I university, Faculty of Law, page 90

በሌላ በኩል የይርጋ ፅንሰ ሃሳብ በሕግ ስርዓት ውስጥ መካተቱ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ያህል የፅንሰ ሃሳቡ መኖር መብት ጠያቂውን በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ በይርጋ ጊዜያት መለያየት፣ ትክክለኛ የይርጋ ጊዜን ባለማወቅ፣ ወይም በቸልተኝነት ምክንያቶች የሕግ ድጋፍና በቂ ማስረጃ እያላቸው በርካቶች መብታቸውን አጥተዋል፡፡ በቁጥር ቀላል የማይባሉ ክሶችም በይርጋ ምክንያት ውድቅ ተደርገው በርካታ መዛግብት ተዘግተዋል፡፡ ክስ አቅርቦ መብትን ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ማስረጃ እና የሕግ ድጋፍ እያለ ተከሳሽን ለመጥቀም ሲባል የይርጋ ፅንሰ ሀሳብ በሕግ ድጋፍ ተሠጥቶት በመካተቱ በርካታ መብት ጠያቂዎችን መብት አሳጥቶ ሕግ ተላላፊዎችን ከኃላፊነት ተጠያቂነት ነፃ ማውጣቱ የማይዋጥላቸው አንዳንድ ሰወች ሊኖሩ ቢችሉም የይርጋ ጽንሰ ሃሳብ ግን በመላው ዓለም በስፋት ተቀባይነት ያገኘ የሕግ ፅንሰ ሀሳብ ለመሆን በቅቷል፡፡

## 3. የይርጋ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች

ምንም እንኳን ሁለቱም አይነት የይርጋ ደንቦች ውጤታቸው የተለያየ ቢሆንም ለሁለቱም የሚያገለግሉ የህግ ድንጋጌወችን በኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ[15] ውስጥ እንመለከታለን፡፡ በፍታብሔር ህጉ 1169(1) መሰረት ስለውሎች በጠቅላላው በሚለው ክፍል ውስጥ ስለ ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ መቋረጥ የተቀመጡት ድንጋጌወች በሙሉ ስለ ይዞታ (ያልነበረ መብት ለሚያስገኝ) የይርጋ ደንብ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም አይነቶች የይርጋ ደንቦች በመሰረታዊ መርሆቻቸው እና በሚያስከትሉት ውጤት የተለያዩ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው ያላቸውን ልዩ ባህሪ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 3.1. ያልነበረ መብት የሚያስገኝ ይርጋ ደንብ (Acquisitive Prescription) መሰረታዊ መርሆች

ከላይ እንደተገለጸው ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ አላማ አንድን ጠያቂ የሌለው ንብረት ለረጅም ጊዜ በይዞታው ይዞ ሌሎች የህግ መከላከያወችን በማሟላት የተጠቀመ ሰው ህግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲያልቅ የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን እድል በመፍጠር በንብረት ባለቤትነት ላይ ሰላምንና መረጋጋትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን የይርጋ ደንብ በፍታብር ህጉ 1168(1) ላይ ተመልክቶ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ ይዞታ የሆነ ሰው የዚህን ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ለ 15 (አስራ አምስት) አመታት በስሙ

[15] የኢትዮጵያ የፍታብሄር ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 165/1952፣ አንቀጽ 1169

ከከፈለ የዚሁ ንብረት ባለቤት ይሆናል። ነገር ግን ንብረቱ የርስት መሬት ከሆነ ጉዳዩ በይርጋ አይታገድም። በተጨማሪም የህብረት ስለሆኑ የእርሻ መሬቶች የሚደነግገው የፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1493 የህብረት የእርሻ መሬቶች (land owned by agricultural community) ለሌላ ሰው መተላለፍ እንደማይችሉ ስለሚደነግግ የህብረት መሬቶችን በተመለከተ በሚቀርቡ ክሶች ላይ የይርጋ ደንብ አይፈጸምም ማለት ነው። በተመሳሳይ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1454 መሰረት ለህዝብ አገልግሎት የተመደቡ ሀብቶች (properties fall under public domain) ለሌላ ሰው አይሸጡም፣ አይተላለፉም። በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1150 መሰረትም የይዞታ መብት ያለው ሰው ከራሱ የይዞታ ጊዜ ላይ ንብረቱን ያስተላለፈለትን ሰው የይዞታ ጊዜ ለመደረብ የሚችለው የንብረቱን ይዞታ ያስተላለፈለት ሰው በይርጋ የራሱ ይዞታ ለማድረግ የሚፈቅድ መብት ሲኖረው ብቻ ነው።

ያልነበረ መብት የሚያስገኙ የይርጋ ደንቦች አብዛኛውን ጊዜ ለክርክር ምክንያት የሚሆኑት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ነው። በመሬት ክርክሮች ዙሪያ የተከናወኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአማራ ክልል ውስጥ ብቻ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ከሚቀርቡት ከሁሉም የክርክር አይነቶች ውስጥ 70 % (ሰባ በመቶ) የሚሆኑት የመሬት ክርክሮች ናቸው።[16] ስለሆነም መሬት የአርሶ አደሮች ህይወት ህልውና መሰረት ስለሆነ በገጠር የእርሻ መሬቶች ላይ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክርክሮችን በተመለከተ የይርጋ ደንቦቹ ያላቸውን ተፈጻሚነት እንዲሁም በይርጋ ደንቦቹ ዙሪያ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የያዛቸውን አቋሞች እና በህግ ምሁራን የሚቀርቡ ትንታኔወችን መመልከቱ ተገቢ ነው።

በሰበር መዝገብ ቁጥር (69291)[17] የሰበር ተጠሪ የሆነችው ወ/ሮ ተዋበች ፈረደ በኦሮሚያ ክልል በጉፋ ወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረች ሲሆን ያቀረበችው ክስ ተከሳሽ የሆነው አቶ ጀማል አማን በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) በ 1020 ብር በወለድ አገድ ውል የያዘውን የእኔን መሬት በፍርድ ሀይል ተገዶ እንዲመልስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው። ተከሳሹ በበኩሉ መሬቱን በተከታታይ ለ 11 (አስራ አንድ) አመታት ያረስኩትና የተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1845 መሰረት በይርጋ ታግዷል በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ

[16] ILA, 2015, Assessment of the implementation of rural land laws in Amhara National Regional State, Institute of Land Administration, A study sponsored by the land administration to nurture development (LAND) of USAID, Unpublished as cited in Dr. Daniel. W. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 223.

[17] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 13፣ መዝገብ ቁጥር- 69291፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2005፣ ገጽ 423- 425

ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4) እና አዋጅ ቁጥር 456/97 መሰረት በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የእርሻ መሬቱን ለማስረከብ የሚዋዋለው ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1845 ላይ የተደነገገው የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም በማለት ወስኗል፡፡ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ትርጉም ትክክለኛ እንደሆነ ያምናል፡፡ ምክንያቱም የወለድ አገድ ዉሉ የተፈጸመው በ 1990 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከወጣ በኋላ ስለሆነና ዉሉ ከህገመንግስቱ ጋር ስለሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል በሰበር መዝገብ ቁጥር (69302)[18] የሰበር ተጠሪ የሆነው አቶ ፈይሳ መንግስቱ በኦሮሚያ ክልል ባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን ያቀረበው ክስ የስር ተከሳሽ (የሰበር አመልካች) የሆነው አቶ ሽልማ ነገሰ በህገወጥ መንገድ የያዘብኝን መሬት እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ መሬቱን መያዙን አምኖ ነገር ግን ከከሳሽ አባት መሬቱ ላይ ያሉትን ዛፎች የገዛኋቸው በመሆኑ  እንዲሁም የከሳሽ አባት ከሸጠልኝ በኋላ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመኖር ስለተዛወረ  መሬቱን በተከታታይ ለ 12 (አስራ ሁለት) አመታት የተጠቀምኩበት ስለሆነ የቀረበው ክስ በይረጋ ስለሚታገድ ልጠየቅ አይገባም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በፍታብሄር ህግ ቁጥሮች 1677 እና 1845 መሰረት ክሱ 10 (አስር) አመት ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 69291 ላይ ከያዘው አቋም የተለየ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሰረቱ በፍታብሄር ህጉ አንቀጽ 1133 ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ዛፎች እና ሰብሎች ከመሬት ሳይለያዩ በሚቆዩበት ጊዜ ከመሬቱ ጋራ እንደ አንድ አካል ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ጽሁፍ የጻፉት ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሲሰጡ የስር ከሳሽ አባት ዛፎቹን ለስር ተከሳሹ በቁም ከሸጡ በኋላ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመኖር መዛወራቸውና የስር ተከሳሹ መሬቱን በተከታታይ ለ 12 (አስራ ሁለት) አመታት ሲጠቀምበት መቆየቱ የሽያጭ ዉሉ ዛፎቹን ብቻ ሳይሆን መሬቱንም ለማስተላለፍ እንደተደረገ ይጠቀማል በማለት ይከራከራሉ፡፡[19]

[18] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 13፣ መዝገብ ቁጥር- 69302፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2005፣ ገጽ 426- 429
[19] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 241

ይህ ደግሞ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4) ጋር ስለሚጋጭና ውሉን ህገወጥ ስለሚያደርገው ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ አይደለም በማለት ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡[20] የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም የዶክተር ዳንኤል ሀሳብ ሚዛን እንደሚደፋ ያምናል፡፡

በሌላ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 71204 (ያልታተመ)[21] የሰበር አመልካቹ የኩታበር ወረዳ ቀበሌ 13 አስተዳደር የስር ከሳሽ የነበረ ሲሆን በአማራ ክልል በኩታበር ወረዳ ፍርድ ቤት የስር ተከሳሽ በሆነው አቶ ሀብቱ ሞላ ላይ ያቀረበው ክስ ተከሳሹ የመንግስትን ቤት በህገ ወጥ መንገድ ለ 29 (ሀያ ዘጠኝ) አመታት የያዘ ስለሆነና ቦታው ለልማት ስለሚፈለግ ቦታውን እንዲለቅ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ አቶ ሀብቱ ሞላ በበኩሉ ቤቱ የተሰጠኝ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የጥበቃ ሰራተኛ ሆኘ ላገለገልኩበት ምትክ (ካሳ) ስለሆነ እና ለ 29 አመታት ያለማቋረጥ የኖርኩበት ቤት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በፌዴራልና በክልሎች የመሬት አዋጆች መሰረት መሬት ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው መንግስት ሲደለድል፣ ወይም ከቤተሰብ ሲገኝ ፣ ወይም በሊዝ ውል አማካኝነት ነው፡፡ ስለሆነም አቶ ሀብቱ ሞላ ለሰጠሁት የጥበቃ አገልግሎት በምትኩ ቦታ ተሰጥቶኛል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ቦታው የተገኘበት አግባብ ህገ ወጥ ስለሆነ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት ወስኗል፡፡

ነገር ግን ምሁራን በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም ላይ የልዩነት ሀሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ዶክተር ዳንኤል አስተያየታቸውን ሲሰጡ ለአቶ ሀብቱ ቦታው የተሰጠው በደርግ ዘመነ መንግስት ጊዜ ሲሆን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የወጣን ህግ ወደ ኋላ መልሶ ተፈጻሚ ማድረጉ ተገቢነት ስለሌለው ጉዳዩ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል፡፡[22] በተጨማሪም ያለ ህግ አግባብ የተያዘን የመንግስት (የህዝብ) መሬት ለማስመለስ የሚቀርብ ክስ በፍታብሄር ህግ ቁጥሮች 1168 (2) እና 1845 መሰረት በይርጋ ሊታገድ ይገባል የሚል አቋም አላቸው፡፡[23]

---

[20] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 240

[21] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ፣ መዝገብ ቁጥር- 71204፣ መጋቢት 10፣ 2004 E.C፣ (ያልታተመ) በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 235 ላይ የተጠቀሰ

[22] Dr. DanielW. Ambaye, የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 241

[23] ዝኒ ከማሁ

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅም በዘመናዊ የህግ ፍልስፍና መሰረት ህጎችን ከወጡበት ጊዜ ወደ ኋላ መልሶ ተፈጻሚ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ያምናል፡፡[24]

በሌላ የሰበር መዝገብ ቁጥር 96203(ያልታተመ)[25] የሰበር ተጠሪ የሆነው የሰሜን አቸፈር መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የስር ከሳሽ የነበረ ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ የስር ተከሳሽ የሆነው አቶ ቸኮል ቁሜ ለ 16 (አስራ ስድስት) አመታት በህገ ወጥ መንገድ ክርክር የተነሳበትን መሬት እየተጠቀመበት ስለሆነ መሬቱን እንዲለቅ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ የስር ተከሳሽ በበኩሉ መሬቱን ያገኘሁት በመሬት ድልድል ወቅት በህጋዊ መንገድ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶኝ ስለሆነና ለ 16 (አስራ ስድስት) አመታት የተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ሊታገድልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሳኔወችን ከሰጡ በኂላ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም የመሬት አስተዳደር ተቋማት ያለአግባብ በግለሰቦች የተያዘ መሬትን ለማስመለስ ሲሉ የሚያቀርቡት ክስ በይርጋ እንዲታገድ የሚደነግግ የመሬት አዋጅ ባለመኖሩ የመሬት አስተዳደር ተቋማት ያለምንም የጊዜ ገደብ ክስ ማቅረብ እንደሚችሉና ጉዳዩ በይርጋ እንደማይታገድ ወስኗል፡፡

ነገር ግን በመስኩ ምርምር ያደረጉ አንዳንድ ምሁራን እንደሚገልጹት አንድ ሰው ከ 15 (አስራ አምስት) አመት በላይ ግብር እየከፈለና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዞ እየተጠቀመበትን ያለ መሬት መሬቱን የተረከብከው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በሚል ምክንያት የሚነጠቅ ከሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ መሬቴን በማንኛውም ጊዜ ልነጠቅ እችላለሁ የሚል ስጋትና አለመረጋጋት (tenure insecurity) ይፈጥራል፡፡[26] ስለዚህ የመሬት አስተዳደር ተቋማት ማቅረብ የሚገባቸውን ክስ በንቃትና በፍጥነት እንዲያቀርቡ ለማስቻልና የህብረተሰቡን ስጋት ለማስወገድ ይረዳ ዘንድ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1168 የተመለከተው የይርጋ ደንብ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ይከራከራሉ፡፡

የገጠር የእርሻ መሬትን በተመለከተ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ 4ኛ (አራተኛ) የፓርላማ ዘመኑ 5ኛ (አምስተኛ) አመት፣2ኛ (ሁለተኛ) መደበኛ ስብሰባ ሠኔ 18 ቀን 2007

---

[24] Deborah k. Mc Knight, Retroactivity of Statutes; What Constitutional limits are there on the retroactive application of laws? , 2005, accessed at www.house.leg.state.com last visited on 12/12/2015, page 8

[25] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ፣ መዝገብ ቁጥር- 96203፣ሚያዚያ 9፣ 2006 E.C፣ (ያልታተመ) በዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 239 ላይ የተጠቀሰ

[26] ዶ/ር ዳንኤል፣ የግርጌ ማስታወሻ 9፣ ገጽ 239

ዓ.ም በሰጠው የህገመንግስታዊ ትርጉም መሰረት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል ህገ መንግስታዊ መብት አላቸው፡፡ ለዚህ ትርጉም መነሻ የሆነው ከኦሮሚያ ክልል የተነሳ የባልና ሚስት የገጠር መሬት ክርክር ነው፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤቶች ጀምራ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበችው ማመልከቻ ተጠሪው የቀድሞ ባለቤቷ መሆኑን በመግለጽ ባጋጠማት የጤና ችግር ምክንያት ክስ ማቅረብ ከሚገባት 12 (አስራ ሁለት) አመታት ዘግይታ ድርሻዋን መሬት እንዲያካፍላት ክስ መሰረተች፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን ይህንኑ መከራከሪያ ነጥብ በመመልከት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ህገ መንግስታዊ ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ 4ኛ የፓርላማ ዘመኑ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሠኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው የህገመንግስታዊ ትርጉም አመልካች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (4) መሰረት ከመሬቷ ያለመነቀል ህገ መንግስታዊ መብት ያላት በመሆኑ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ሊታገድባት አይገባም፡፡[27]

### 3.2. የግዴታ አስቀሪ ይርጋ ደንብ (Liberative Prescription) መሰረታዊ መርሆች

ከዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ ባለመብቱ መብቱን ሳይጠይቅ በህግ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን የሚያሳጣ የይርጋ ደንብ ነው፡፡ ከስሙ እንደምንረዳው ይህ የይርጋ ደንብ የሚያገለግለው በግዴታ ህግ ውስጥ ነው፡፡ የይርጋ ደንቡን አስመልክቶ በተለያዩ ሕጎች ውስጥ የተካተቱት ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያመላክቱት ክስ ለማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንዲቻል በሕግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብም እንደጉዳዩ ክብደት፣ ባሕሪና ሁኔታ የተለያየ ሲሆን ለሁሉም ጉዳዮች የተቀመጠ ተመሣሣይ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የለም፡፡ በመሆኑም ሕግ አውጪው እንደ ጉዳዩ ዓይነት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንደሚቻል ለማመላከት የተለያዩ የክስ ማቅረቢያ ጊዜወችን በሕጎች ውስጥ እንዲካተት አድርጓል፡፡ ክስ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በሕግ ውስጥ ከተካተተ በኋላ ሌላው ሊነሳ የሚገባው ሀሳብ የተቀመጠው የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ከመቼ ወይም ከምን ሁኔታ ጀምሮ መቆጠር እንደሚጀምር ማመልከት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት በኢንሹራንስ

[27] በዚህ ጭብጥ ዙሪያ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በቁጥር በርከት ያሉ ህገ መንግስታዊ ትርጉሞችን የሰጠ በመሆኑ ትርጉሞቹን መመልከት ይቻላል፡፡

ውል ምክንያት የሚቀርብ ክስ መቅረብ ያለበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ መገለፁ እንደጥሩ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል፡፡[28]

በተጨማሪም በሕግ ላይ የተገለጸው ክስ የማቅረቢያ ወይም መብት የመጠየቂያ ጊዜ እንደ ጉዳዩ እና ሕጉ ልዩ ባህሪ በሚመለከታቸው አካላት በውል ሊያጥር ወይም ሊረዝም ስለሚችልበት ሁኔታ በህጉ ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡ በህጉ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜን ማሻሻል እንደሚቻል ወይም እንደማይቻል በህጉ ማመላከት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ይርጋን አስመልክቶ ተጨማሪ መብት እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው ከማስገንዘብ ባለፈ መብቱ በሕግ ከተሰጠ የይርጋ ጊዜን የማሻሻል ዕድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በንግድ ሕጋችን መሰረት በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት እና የይርጋ ጊዜውን ተዋዋይ ወገኖች በውል ለማሣጠር እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ ይህም የሚያመላክተው የኢንሹራንስ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሕጉ የተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት በውል ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡[29]

በሕግ የተቀመጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ሊቋረጥና የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደ አዲስ ሊጀመር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ከይርጋ ደንብ ጋር ተያይዥ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው፡፡[30] ለምሳሌ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ ውል እንዲፈጸም ወይም ካለመፈፀሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊጠየቅ እንደሚገባ የተመለከተ ሲሆን በቁጥር 1851 እና 1852 መሰረት በአስር ዓመት ጊዜው ውስጥ ለምሳሌ በዘጠነኛው አመት ላይ ባለዕዳው ዕዳውን ካመነ፣ በከፊል ከከፈለ፣ መያዣ ወይም ዋስ ከሠጠ ወይም ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት ለፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለባለዕዳው አስታውቆ እንደሆነ ይርጋው ሊቋርጥ እንደሚችልና ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደገና እንደ አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር እንደሚጀመር በግልፅ የተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

---

[28] የኢትዮጵያ የንግድ ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 166/1952፣ አንቀጽ 674(1)
[29]ዝኒ ከማሁ፣ የንግድ ህግ አንቀጽ 674(3)
[30] ጥላሁን ተሾመ የግርጌ ማስታወሻ 4

### 3.3. የይርጋ መከራከሪያን ሊያነሳ የሚችለው ማን ነው?

በወንጀል ጉዳይ ላይ ይርጋን በመቃወሚያነት አንስተው ለመከራከር የሚችሉት ተከሳሽ፣ ዐቃቤ ሕግና ፍርድ ቤቶች ስለመሆናቸው በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ[31] አንቀጽ 130 ስር ተመልክቷል። በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ[32] አንቀጽ 216 (2) መሰረት የወንጀል ክሱ በይርጋ ስለመታገዱና ክሱን ለመቀበል የማይገባ ስለመሆኑ ተከሳሹ ባያመለክትም አቃቤ ህግ ወይም ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ የይርጋ መቃወሚያውን የማንሳት ሀላፊነት አለባቸው። ስለሆነም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ እና በወንጀል ህጉ መሠረት በመዝገቡ ላይ ሕጋዊ አስተያየት በሚሠጥበት ወቅት ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆን አለመሆኑ የመረዳትና ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ከሆነም በይርጋ ምክንያት ክስ አያስቀርብም በሚል መዝገቡን የመዝጋት ኃላፊነት እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል። በአንጻሩ ግን ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ በተከራካሪ ወገኖች በኩል ይርጋ በመከራከሪያነት ባልቀረበበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ይርጋን እንደ አንድ የመከራከሪያ ነጥብ አንስተው ሊመረምሩ ይችላሉ ወይ? የሚለው ነጥብ ተያይዞ ሊነሳ ይገባል።

የፍትሐብሔር ስረ ነገር (ፍሬ ጉዳይ) የይርጋ ደንቦችን (substantive period of limitation) በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1856(2) ሥር እንደተመለከተው ዳኞች በተከራካሪወች ካልተነሳ በቀር በገዛ ሥልጣናቸው የይርጋውን ደንብ በመቃወሚያነት ለመጥቀስ አይችሉም በሚል የተመለከተ በመሆኑ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፍርድ ቤቶች የይርጋ መከራከሪያ በተከራካሪ ወገኖች ካልተነሳ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጊዜ ይርጋን በመከላከያነት ሊያነሱና ሊወስኑ አይችሉም።

ነገር ግን በሥነ ሥርዓት ሕጎች የተደነገጉ የይርዳ ደንቦችን (procedural period of limitation) በተመለከተ በኢትዮጵያ የፍታብሀር ሥነ ሥርአት ህግ[33] ቁጥር 49 ስር እንደተደነገገው በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረ የይርጋ ጊዜን በማሳለፍ የሚቀርብ ጥያቄን ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ ይችላል። በዚሁ ጉዳይ ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ አንድ ላይ በሚገኘውና በመዝገብ ቁጥር 17361[34]

---

[31] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1954፣ አንቀጽ 130(2)(ሐ).

[32] የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996፣ አንቀጽ 216(2)

[33] የኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/1958፣ አንቀጽ 49

[34] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 1፣ መዝገብ ቁጥር- 17361፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 1997፣ ገጽ 12

በሰጠው ውሳኔ ላይ በሥረ- ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ መሆናቸውን እና በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ እንዳለበት ወስኗል። የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244(2) ላይ ይርጋን ጨምሮ የሚቀርቡ ሌሎች የክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ምክንያቶችን ተከራካሪ ወገኖች ሊያቀርቡ ይችላሉ በሚል የሚያስቀምጥ ቢሆንም ከተለመደው አሰራርና ሁኔታ ለመረዳት እንደሚቻለው ይርጋን በመቃወሚያት የሚያቀርበው ክስ የቀረበበት ወገን (ተከሳሽ) ነው። ምክንያቱም ከሳሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበው ክስ በይርጋ እንደሚታገድ ቢያውቅም እንኳን የራሱን ክስ ውድቅ ለማስደረግ ፍላጎት አይኖረውም። ነገር ግን በፍትሐብሔር ጉዳይ ከሳሽ የሆነ ወገን ይርጋን በመከራከሪያነት ሊያነሳ የሚችለው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 በተቀመጠው መሰረት ከተከሳሽ ወገን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብበት ነው።

ጠበቃወች የደንበኞቻቸውን ጉዳዮች በሚመለከቱበት፣ የክስ መልስ በሚሠጡበት እንዲሁም ክርክር በሚያደርጉበት ወቅት ይርጋን አስመልክቶ የተጣለባቸው ሕጋዊ ኃላፊነት አለ። በጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 25 መሠረት ጠበቆች በሕግ የተቀመጡትን የይርጋ መቃወሚያወች በመከራከሪያነት ማንሳት እንዳለባቸው በአስገዳጅነት ተመልክቷል። ጠበቆች የደንበኞቻቸውን ጉዳይ ይዘው በሚከራከሩበት ወቅት ለደንበኞቻቸው በሕግ የተፈቀደላቸውን የይርጋ መቃወሚያወችን ሳያቀርቡ ሊቀሩ የሚችሉት ሁኔታውን ለደንበኞቻቸው በግልጽ ካስረዱ በኋላ ደንበኞቻቸው ይርጋን በመከራከሪያነት እንዳያቀርቡ በጽሑፍ ፈቃዳቸውን ሲሰጧቸው ብቻ እንደሆነ በስነ ምግባር ደንቡ ተመልክቷል። ነገር ግን ጠበቆች በሕጉ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ የደንበኞቻቸውን ልዩ ፍቃድ በጽሑፍ ሳያገኙ ቀርተው ይርጋን በመከራከሪያነት ሊያቀርቡ እየተገባቸው በመከራከሪያነት ሳያቀርቡ ቢቀሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 24(3) ሥር የተመለከቱትን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከማግኘት እስከ ጥብቅና ፍቃድ መሰረዝ የሚደርሱ የተለያዩ ቅጣቶችን ሊቀጡ ይችላሉ።

### 3.4. ይርጋ በመከራከሪያነት የሚነሳው መቼ ነው?

በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተከራካሪው (ተከሳሽ) ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 234 መሰረት ለቀረበው ክስ (አቤቱታ) የመከላከያ መልስ በጽሑፍ ሲሰጥ መሆን እንዳለበት በስነ ስርአት ህጉ አንቀጽ 244(2)(ሠ) ላይ ተመልክቷል።

እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ ለፍርድ ቤቱ ማንነቱን ካስመዘገበና ክስ ከተነበበለት በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክስና መከራከሪያ ከመቅረቡና ማስረጃም ከመሠማቱ በፊት ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 130(2)(ሐ) እና (3) ላይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ይርጋን በመቃወሚያነት ማቅረብ የሚቻለው ክስ ከመሰማቱ እና ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር በተከሳሽ በኩል ተፈፅሟል አልተፈፀመም የሚለው ነጥብ ላይ ክርክር ከመደረጉ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ነው፡፡

### 3.5. በይርጋ ደንብ የማይታገዱ ጉዳዮች

ለአብዛኛዎቹ የህግ ጉዳዮች ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ተቀምጦላቸዋል፡፡ ሆኖም ጥቂት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ሳይኖር ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም የጊዜ ገደብ በማንኛውም ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚቻልባቸው ጉዳዮች እንዳሉ በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተመልክቷል፡፡ የሽብርተኝነት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡[35] በዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶች ውስጥ በጦር ወንጀሎች እና በሰብዓዊነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ የይርጋ ደንብ እንዳይፈፀም በተደረገው ስምምነት መሰረት የዘር ማጥፋት፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንዲሁም የጦር ወንጀሎችን የሚፈፅሙ ሰዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶች በይርጋ አይታገዱም፡፡[36] በተጨማሪም ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሰረት በአዋጁ የተመለከቱ ከሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር የተገናኙ ወንጀሎችን በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡[37] ከላይ የተጠቀሱት ወንጀሎች በይርጋ የማይታገዱበት ምክንያት በጣም አደገኛና የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብትና ክብር የሚነኩ በመሆናቸው ነው፡፡

በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 10 የሰበር መዝገብ ቁጥር 43600 ላይ በሰጠው ውሳኔ[38] መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ ባለመብት የሆነው ሰው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1206 መሰረት መብት ሳይኖረው በእጁ ካደረገው ሌላ ሰው

---

[35] የኢፌዴሪ የጸረ- ሽብርተኛነት አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 24

[36] William .P. Anson, Principles of English Law, 19th ed. 1945, Oxford University Press, p. 67.

[37] ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ የኢፌዴሪ አዋጅ ቁጥር 909/2007፣ አንቀጽ 25

[38] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር- 43600፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2003፣ ገጽ 224

ወይም ከያዘው ሰው ላይ ሃብቱ ይገባኛል ሲል የሚያቀርበው የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይችልም፡: በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1678፣ 1716 እና 1718 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 14 የሰበር መዝገብ ቁጥር 79394[39] እና በቅፅ 12 የሰበር መዝገብ ቁጥር 43226 ላይ በሰጣቸው የህግ ትርጉሞች መሰረት የውል መሠረታዊ ዓላማ በሕግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች/ዳኞች ሕገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ሕገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

## 4. የይርጋ ደንብ በኢትዮጵያ አበይት ህግጋት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (የፌ/ጠ/ፍ/ቤት) ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ደንብ ትርጎሞች

### 4.1. የውል ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1845 መሠረት ውል አልተፈፀመልኝም በሚል ምክንያት እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው ወይም ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ሰው ክሱን ማቅረብ ያለበት ውሉን አልፈፀምም ከተባለበት ወይም ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን በአንቀጹ ላይ "ህግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር…" የሚለው ሀረግ ልዩ ውሎችን የሚመለከቱ የተለዩ የይርጋ ጊዜ ገደቦች ካሉ አጠቃላይ የይርጋ ደንቡ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይጠቁማል፡፡ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1852 መሰረት የይርጋ ማቋረጥ ውጤት ይርጋውን እንደገና እንደ አደስ መቆጠር እንዲጀምር ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ህግ አንቀጽ 2024(መ) መሰረት ለቤቶች ኪራይና ለ እርሻ ሀብት ለሆነ የሚከፈል እዳን በተመለከተ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ 2 (ሁለት) አመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ባደረገው ጥናት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከ ቅጽ አንድ ጀምሮ እስከ ቅጽ አስራ ሰባት ድረስ ይርጋን በተመለከተ የወሰናቸው ውሳኔወች በቁጥር 70 (ሰባ) ያህል ሲሆኑ ከነዚህ ውሳኔወች ውስጥ በቁጥር 21 (ሀያ አንድ) ወይም ሰላሳ ከመቶ (30%) የሚሆኑት የውል ህግን የተመለከቱ የይርጋ ደንብ ትርጎሞች ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር

[39] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 14፣ መዝገብ ቁጥር- 79394፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2006፣ ገጽ 199

ሰሚ ችሎቱ በውል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) በሰንጠረዥ መልክ እናያለን፡፡

## ሰንጠረዥ 1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ. ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ (volume) ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ዓሊ ቃሴብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ | 19081 | ቅጽ 4 | በውል ባለእዳ የሆኑ ባለ እዳወች ሁሉ እዳው በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን መከራከር ይችላሉ፡፡. ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳው የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1901 |
| 2. | ወ/ሮ ወርቅነሽ አርምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ | 29363 | ቅጽ 8 | መህይምነትን ወይም አይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719፣ 1845 |
| 3. | ወ/ሮ ሀጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አልዩ | 34940 | ቅጽ 8 | ክርክር የሚካሄድበት የውል ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አለው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣ 1845 |
| 4 | እነ አቶ ወልደፃድቅ ብርሃኑ እና አቶ ስንታየሁ አያሌው | 38935 | ቅጽ 8 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዱፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ 10 (አስር) አመት ይርጋ ይታገድበታል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1)፣ 1732፣ 1789 እና 1845 |
| 5. | አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ | 36756 | ቅጽ 8 | በፍታብሔር የውል ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከሳሽ ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 |
| 6. | እነ ወ/ሮ | 39725 | ቅጽ 8 | የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ሻጭን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አለምሸት ካሣሁን እና አቶ ሽመልስ እንዳለ | | | የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3) |
| 7. | አቶ አብዱራዛቅ ሀሚድና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | 44800 | ቅጽ 10 | በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 |
| 8. | ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል | 43636 | ቅጽ 10 | ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845፣ 1851 |
| 9. | እነ ሙና እንድሪስና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | 48094 | ቅጽ 10 | አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 |
| 10 | እነ ሙለጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ | 46019 | ቅጽ 10 | የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት አይሸፈንም፡፡ የፍ/ብ/ሔ/ቁ. 2024 |
| 11 | እነ ፍስሀ መንግስቱ ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሀ | 42346 | ቅጽ 10 | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1)፣ 2464(1)፣ 2441(1) |
| 12 | አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ | 42691 | ቅጽ 10 | የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1)፣ 1845 |
| 13 | መሐዳ ይመር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | 55229 | ቅጽ 12 | አንድን እቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው እቃ ጉድለት አለበት በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ አመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291፣ 2292፣ 2298(1) |
| 14 | ኡመር ከድር እና በዳዳ ሰቦቃ | 48012 | ቅጽ 12 | በፍ/ብ/ህ/ቁ 1810 (2) ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈጻሚ የሚሆነው ዉሉ በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1810 (2) |
| 15 | እነ ንግስት ኪዳኔ እና በለጠ ወልደሰማያት | 67376 | ቅጽ 13 | ወካይ የሆነ ወገን በተወካይ አማካኝነት የተደረገን ህገ ወጥ ውል እንዲፈርስ በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በ አስር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2187፣ 2198፣ 1810፣ 1808 (1)፣ 1845 |
| 16 | ጀማል አማን እና ተዋበች ፈረደ | 62291 | ቅጽ 13 | በወለድ አገድ ውል (contract of Antichresis) አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የእርሻ መሬቱን ለማስረከብ የሚዋዋለው ውል ህገ ወጥ ስለሆነ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 (3)(4)፣ አወጅ ቁጥር 456/97 |
| 17 | አቶ ሽለማ ነገሰ እና ፈይሳ መንግስቱ | 69302 | ቅጽ 13 | መሬት ላይ ያሉትን ዛፎች በውል የሸጠ ሰው መሬቱ እንዲለቀቅለት በ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 መሰረት በ 10 አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ |
| 18 | የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ድርጅት እና ባርጉባ ትሬዲንግ | 80642 | ቅጽ 14 | በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አንገፍ ለውሉ ምክንያት የሆነው ንብረት ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ እቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ ይታገዳል፡፡ የባህር ህግ ቁ. 146፣ 203. የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1826፣1828፣1829 (ሀ). |
| 19 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ጥጋቡ ተፈራ | 78444 | ቅጽ 14 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በማያዣው ላይ ያለው መብት በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር አመት ከማለፉ በፊት የመያዣ መብቱን መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1) (3) |
| 20 | አብደላ ኢብራሂም እና ኡሶ አብዲ | 79394 | ቅጽ 14 | የውሉ መሰረታዊ አላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ አዋጅ ቁጥር 130/99፣ አዋጅ ቁጥር 89/89- አንቀጽ 2 (3)፣ አዋጅ ቁጥር 456/97- አንቀጽ 8 (2). |
| 21 | አንበሳ ኢንሹራንስ | 98358 | ቅጽ 17 | የባህር ላይ የእቃ ማጓጓዝ ውልን በተመለከተ የዕቃው ርክክብ ከተፈፀመበት ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ኩባንያ እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት | | | እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የባህር ህግ ቁጥር 203፤180፤162 |

## 4.2. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ የይርጋ ደንቦች

የኢፌዴሪ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/88 አንቀጽ 162 ስንመለከት አንድ በህገ ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተ ሰው በዚህ መሠረት ወደ ስራው እንዲመለስ ለመጠየቅ የሚችለው ስራው ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ በይርጋ መብቱን ያጣል፡፡ ከህገ ወጥ ስንብቱ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ የካሣ ክፍያዎች እና ሌሎች ተያያዥ የክፍያ ጥያቄዎችን ለማግኘት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄዎቹ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡ ከነዚህ ከላይ ከተገለጹት ውጪ የሆኑ ከስራ ውል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ደግሞ የሥራ ውል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ የደሞዝ፣የትርፍ ሰአትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ ክፍያው በተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ የሥራ ውል በመቋረጡ የተነሳ በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ ከላይ ከተገለፁት ምክንያቶች ውጪ ሌሎች ከቅጥር ውል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ማቅረብ የሚቻለው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈም በዚህ ጠቅላላ ደንብ ያልተሸፈነ ጉዳይ ሲያጋጥም አግባብ ያለው ህግ በማሟያነት እንደሚያገለግል ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በፍትሐብሄር ጉዳይ የፍትሐብሄር ህግ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የተቀመጡት የይርጋ ደንቦች ከሌሎች ህጎች አንጻር ሲታዩ የጊዜ ገደባቸው አጭር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በባህሪው ጥንቃቄን የሚሻ፣ የኢንዱስትሪውን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ አለመግባባቶች ተንጠልጥለው ሳይቆዩ በአፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/88 መግቢያ ላይ የተቀመጡት "…. የኢንዱስትሪ ሰላምን በመፍጠር… በመተባበር በጋራ እንዲሠሩ ማድረግ ጠቃሚ በመሆኑ… የሥራ ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሔ

እንዲያገኝ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ…” የሚሉት ሐረጎች የሚጠቁሙትም ይህንኑ ነው፡፡ ስለሆነም የይርጋ ጊዜን የተመለከቱት ድንጋጌዎች ከዚህ አጠቃላይ መንፈስ አንፃር መታየት ይገባቸዋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 163 ላይ እንደተገለፀው በአዋጁ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የአንድ መብት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በምሳሌ ለመግለጽ ያህል አንድ ሠራተኛ ከሥራ የተሰናበተበት ዕለት ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ቢሆን ያላግባብ ከስራ ተሰናብቻለሁና ወደ ሥራ ልመለስ ቢል በዚህ መብቱ መጠቀም የሚችለው ከሥራ ስለመሰናበቱ በደብዳቤ ከተገለጸለት ዕለት ጀምሮ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው መታሰብ የሚጀምረው ግን በመብቱ ለመጠቀም ከሚችልበት ደብዳቤ ከደረሰው ዕለት ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ቀን ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የዋለው ሥራ በማይሠራበት የበዓል ዕለት ቢሆን እንኳ አቆጣጠሩን ከመጀመር አንፃር የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ነገር ግን የይርጋውን መቆጠር ማብቂያ ጊዜ ከማስላት አኳያ የመጨረሻው ዕለት ሥራ በማይሠራበት ዕለት ከዋለ ሥራ የሚሠራበት ተከታዩ ቀን የመጨረሻ ማብቂያው ጊዜ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የወንጀል ጉዳይ ግን የይርጋው ጊዜ መታሰብ የሚጀምረው ጥፋተኛው የወንጀል ድርጊቱን ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ሲሆን ጥፋቱ እየተደጋገመ የተፈፀመ እንደሆነ የወንጀሉ ድርጊት መፈፀም ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ የይርጋው ጊዜ መታሰብ ይጀምራል፡፡

ከዚህ በመቀጠል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የይርጋ ገደቦችን ሊያቋርጡ የሚችሉ ምክንያቶች እንመለከታለን፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164(1) መሰረት ጉዳዩ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ይሆናል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን በስራ ላይ ለማዋልና ለማስፈፀም ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜም ይርጋን የሚያቋርጥ ምክንያት ነው፡፡ (አንቀጽ 164(2))፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን በስራ ላይ ለማዋልና ለማስፈፀም ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ማነው ብለን ስንጠይቅ በአዋጁ አንቀጽ 12(6)፣ 20፣ 21፣ 89፣ 138(መ)፣ 178፣ 179 መሰረት ከዳኝነት ሰጭነት ሀላፊነት በተጨማሪ አስተዳደራዊ በሆነው ነገር ላይም አዋጁን የሚያስፈጽሙት አካላት ባለስልጣን ሊባሉ ይችላሉ፡፡ የይርጋ ጊዜ መቋረጥ የሚያስከትለው ውጤት በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ ላይ አልተገለፀም፡፡ ነገር ግን በአዋጁ ድንጋጌዎች ላይ ባልተሸፈነ የይርጋ ጉዳይ

አግባብ ያለው ህግ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው በአንቀጽ 162(5) ላይ የተገለፀ በመሆኑ ለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለውን የፍትሐብሔር ህግ በማሚያነት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች በሰንጠረዥ መልክ እንመለከታለን፡፡

## <u>ሰንጠረዥ 2</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/ | 16648 | ቅጽ 3 | • የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜ በአዋጅ 377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/3/ ስር በተቀመጡት የይርጋ ድንጋጌዎች ይመራል፡፡<br>• የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሰራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የራሳቸውን መብት መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ጥያቄ በአዋጅ ቁ./377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/4/ በተደነገጉት ሳይሆን በአንቀጽ 162/1/ በተደነገገው የይርጋ ድንጋጌ ይመራል፡፡<br>• በአዋጅ ቁ./377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቆመው ክሱ በአዋጅ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን በተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በፍርድ ቤቶች በተቋቋሙ የስራ ክርክር ችሎቶች የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡<br>• ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባልተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በስራ ክርክር ችሎት የቀረበ ክስ በአዋጅ ቁ. /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜን መቆጠር አያቋርጥም፡፡ በአዋጅ ቁ. 377/96/ አንቀጽ 164/2/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው አቤቱታው የቀረበው ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ለአሰሪ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | የቀረበ አቤቱታ በአዋጅ ቁ. 377/96) አንቀጽ 164(2) መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጥም፡፡ |
| 2. | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሀመድ አደን | 37573 | ቅጽ 8 | ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን አያቋርጥም፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/2/ |
| 3. | ጉደር አግሮ ኢንደስትሪ እና አቶ በለጠ ጫላ | 45746 | ቅጽ 9 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጎ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውለን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ነው፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3) |
| 4. | ኤርፖርቶች ድርጅትና ሶፋኒት | 51912 | ቅጽ 9 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት አይደለም፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2) |
| 5. | ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አማረ ገላው | 36730 | ቅጽ 9 | ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሄድ የይርጋ ጊዜን ያቋርጣል፡፡( ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎቱ በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም ተለውጧል)፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138፣ 147፣ 164(1) |
| 6. | ጉልላት ወልዴ እና ጅምላ ሸቀጦች ድርጅት | 63635 | ቅጽ 11 | በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር አሰሪው ሰራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የጻፈው ደብዳቤ ሰራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ ያቋርጣል፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 164(3)፣ ፍ/ብ/ህግ ቁ. 1852(1). |
| 7. | ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና በዳሶ መልካቶ | 53527 | ቅጽ 11 | በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈጸም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ |
| 8 | ኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት ኮሌጅና ዶ/ር ደሣለኝ ተመስገን | 96458 | ቅጽ 16 | የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ይታገዳል፡፡ የጳጉሜ ቀናት በይርጋ ቀናት ሊካተቱ አይገባም፡፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4)፣የፍ/ሕ/ቁ. 1860(3) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | አቶ ዳዊት ገ/ማርያም ና ሣህለማርያም ደግፌ | 101020 | ቅጽ 17 | በሠራተኛው የሚጠየቅ የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በአሠሪው የይርጋ መቃወሚያ ካልቀረበበት በስተቀር ለሰራኛው ሊከፈል ይገባል፡፡ |

## 4.3. የውርስ ህግ የይርጋ ደንቦች

ውርስን በተመለከተ የተለያዩ የጊዜ ገደቦች ተደንግገዋል፡፡ የኑዛዜን መፍረስ የሚፈልጉ ወገኖች ይህን መብት የሚጠቀሙት ኑዛዜው ከተነበበ ወይም መነበቡን ካወቁና ተቃውሚቻውን በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለውርስ አጣሪው ከገለፁ በኂላ ባሉት ቀጣይ ሶስት ወራት ውስጥ እንደሆነና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ግን ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ማቅረብ እንዳለባቸው የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥሮች 973 እና 974 ያስገነዝባሉ፡፡ ያለአግባብ የውርስ ንብረት ከያዘ ሰው ላይ ንብረት ለማስመለስ የፈለገ ከሳሽ የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ባወቀ በ ሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ክሱን ማቅረብ እንደሚገባው በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 1000 (1)ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ከሳሹ ይህን ጉዳይ አወቀም አላወቀ ከሳሹ መብቱን መጠቀም ከቻለበት ወይም ሟቹ ከሞተበት ጊዜ አንስቶ አስራ አምስት አመት ካለፈ የውርስ ንብረት ለማስመለስ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል የዚሁ ህግ ቁጥር ቁጥር 1000 (2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል  ሰበር ሰሚ ችሎት በውርስ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች  (ትርጉሞች) በሰንጠረዥ መልክ እንመለከታለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 3</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውርስ  ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | እነ የሻረግ መንግስት እና የሻረግ ፈረደ | 15631 | ቅጽ 3 | ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ባለይዞታ በመሆን የ ቤቱን ግብር ባለማቋረጥ ከ15 ዓመት በላይ በሥሙ ሲከፍል የቆየ ሰው በሕጉ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ ቁ. 1001/2/፣ 1168፣1845፣ 1853 |
| 2. | የገነት ዳምጤ | 38152 | ቅጽ 8 | በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) አመት ጊዜ ውስጥ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው | | | ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ- 1677(1)፣ 1000፣ 1845 |
| 3. | ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ | 40418 | ቅጽ 10 | የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ መብት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልታወቀ ሟች ከሞተበት ቀን ጀምሮ በ አስር አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3) |
| 4. | እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደ መስቀል እና አቶ ስዩም ክፍሌ | 38533 | ቅጽ 10 | የወራሽነት መብትን በህግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይችላሉ፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996፣ 1000(1)፣ 1000(2)፣1060፣1062 |
| 5. | እነ ፀሀይ ሀይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈለቃ ቤኛ | 44025 | ቅጽ 10 | ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጁ አድርጎ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ አይታገድም፡፡ |
| 6. | እነ በላቸው አስፋው እና መኪያ አወል | 47201 | ቅጽ 11 | ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቱ ይለቀቅልኝ በሚል በሚያቀርበው ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ |
| 7. | ቀለሟ ወርቅነህ እና ሻምበል ጌታሁን | 49359 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብትን አስመልክቶ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1851(ለ) መሰረት ሊቋረጥ ይችላል፡፡ |
| 8 | እነ ሀዲስ አ/ስላሴ እና ብሌን አ/ስላሴ | 53223 | ቅጽ 11 | በኑዛዜ ላይ የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው መከፈቱን ያወቀ በ አስራ አምስት ቀን ውስጥ ያላወቀ ደግሞ ኑዛዜው ከተከፈተበት ወይም ሟች ከሞተበት ቀን ጀምሮ በ አምስት አመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡<br>በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 973፣ 974 |
| 9 | ሀና ጸጋየ እና ጣእሙ ደስታ | 57114 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብት ወራሽ የሆነና አካለ መጠን ያላደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለ መጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 |
| 10 | ውለታ ደስታና እቴቴ ደስታ | 52407 | ቅጽ 11 | የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በ ሶስት አመት ይርጋ ይታገዳል፡፡የውርስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተያዘበት ጊዜ እንጂ ስመ ንብረቱ ከተዛወረበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ |

## 4.4የፍታብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐብሔር ስነ -ስርዓት ህግ ውስጥ መብት ሊያሳጡ የሚችሉ የይርጋ ደንቦች ተካተዋል፡፡ በፍትሀብሄር ጉዳይ ላይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ ይግባኝ በ60 ቀናት ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ስነስርዓት ህግ አንቀጽ 323(2) ይገልፃል፡፡ ነግር ግን ሌሎች ህጎች የደነገጉት የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ካለ የፍታብሄር ስነ ስርአት ህጉ የደነገገው የ 60 ቀን የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ስለ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በማንኛውም የስራ ክርክር የቋሚ ወይም የጊዜአዊ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኝ ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ የሚችለው የቦርዱ ውሳኔ በይፋ ከተነበበ ወይም ለተከራካሪ ወገኖች ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር እንዲታረም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በዘጠና ቀናት ውስጥ ነው፡፡[40] ለቃል ክርክር ፍርድ ቤቱ ይዞት በነበረ ቀጠሮ በመቅረቱ የተነሳ መዝገቡ የተዘጋበት ከሳሽ አሳማኝ ምክንያት አቅርቦ መዝገቡን ማስከፈት የሚችለው መዝገቡ ከተዘጋበት ጊዜ ጀምሮ በ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ በፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 74(2) ላይ ተደንግጓል፡፡

ይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ስለመሆኑ የፍታብሄር ስነ ስርአት ህግ አንቀጽ 244(ረ) ይደነግጋል፡፡ በኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 49 መሰረት በፍታብሄር ክርክር ከሳሽ ክርክሩ ሳይጠናቀቅ ከሞተ የክሱ መብት በህጉ አግባብ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚል ወገን ከሳሹ በሞተ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድለት ለፍርድ ቤት ካመለከተ ብቻ ነው፡፡[41] የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49(1) ከሣሽ ሲሞት የክሱ መብት ለሌላ የሚተላለፍ የሆነ እንደሆነ የሟቹ ንብረት አስተዳዳሪ ተተክቶ ክሱን ሊቀጥል እንደሚችል የሚፈቅድ ሲሆን የዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁጥር ሁለት ክሱን ለመቀጠል መብት አለን የሚሉት ወገኖች ዋናው ከሣሽ ወይም ከሣሾች በሞቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል በፍትሀብሔር ሥነ-

[40] የኢ.ፌ. ዲ. ሪ. ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 25/88፣ ሁለተኛ አመት፣ ቁጥር 13፣ አንቀጽ 22(4)

[41] በኢትዮጵያ የፍታብሄር ስነ-ስርአት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/58፣ አንቀጽ 49(1) እና (2)

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 232(1) መሰረት ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ክስ ፎርማሊቲ አላሟላም በሚል ምክንያት በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ውድቅ የተደረገበት ከሳሽ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ክሱ ተቀባይነት ካጣበት ቀን ጀምሮ ለፍርድ ቤቱ በ 5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

የፍትሀብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የሙግትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን አስቀምጧል፡፡ ይኸው ሕግ ያስቀመጣቸውን የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በሚመለከትም በሥነሥርዓት ሕጉ ምእራፍ ሰባት በርካታ ድንጋጌዎችን አሉ፡፡ የሕጉ ቁጥር 192 በአንድ ክርክር ላይ መፈፀም ወይም መደረግ የሚገባው ነገር ሲኖርና ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ በሕግ ያልተወሰነ ሲሆን የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚታየውን ጊዜ ይወስናል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሙግት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በሕግ በተቀመጠው ወይም ፍርድ ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ቁጥር 195 አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል በማለት በተወሰነ የጊዜ ገደብ መፈፀም ያለባቸው ተግባራት ሕጉ ወይም ፍ/ቤቱ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ከተከናወኑ ብቻ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡[42] በመሆኑም በሥነ-ሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በአንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎችን ጥቅም፣ በፍርድ ቤት መኖር ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

የጊዜ ገደቦች አለመከበር ለመዘግየት፣ ለጉዳዮች መከማቸትና መጨናነቅ ምክንያትም ስለሚሆን የሚጎዳው በአንድ ሙግት የሚሳተፉትን ብቻ ሳይሆን የሌሎች የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች መብትና ጥቅምም ይነካል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሙግት ሂደት ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግ ደግሞ ከተከራካሪዎችም የሚጠበቅ ቢሆንም በዋናነት ግን የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህን ሃላፊነት እንዲወጣ ከሚያደርጉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በስነ ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩት የጊዜ ገደቦች በአግባቡ መፈፀማቸውን መከታተልና ያልተፈፀሙ ሆነው ሲገኙ ደግሞ ህጉ እንደሚያዘው ተመጣጣኝ የሆነ ርምጃ መውሰድ ነው፡፡

[42] ዝኒ ከማሁ መግቢያውን ይመልከቱ

በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፍትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረውና የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ በፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው እሱ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ተከራካሪ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ በተከራካሪ ወገን ባይነሣ ቢቀር እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነ-ሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረጉ ትክክለኛው አካሄድ መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጠቁሟል፡፡[43] በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎቱ ፍታብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ 4. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍታብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ጋዲሴ አርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ | 17361 | ቅጽ 1 | በሥረ ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው፡፡ በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 49፣ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1856 |
| 2. | በዛብህ አበበ እና የመንግስት | 35018 | ቅጽ 8 | የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ ምክንያት የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ 10 (አሥር) አመት |

[43] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 1፣ መዝገብ ቁጥር- 17361፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 1997፣ ገጽ 12

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቤቶች ኤጀንሲ | | | ይርጋ ካልታገደ በስተቀር ባለ መብቱ አፈጻጸሙን ማንቀሳቀስ ይችላል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 384 |
| 3. | ሽመልስ አማረ እና አማረ መኮንን | 76601 | ቅጽ 13 | በ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ ይነሳልኝ በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በህጉ የተመለከተው የ አንድ ወር የጊዜ ገደብ በፍታብሄር ህጉ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌት መሰረት መሰላት ይኖርበታል፡፡<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78፣ 195 የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1848፣ 1856(2) |
| 4 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ፈቃዱ ተስፋየ | 74898 | ቅጽ 13 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384 ስር የተመለከተው የ 10 አመት ይርጋ ገደብ የፍርድ ባለመብት ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቆይቶ ፍርዱን ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ |
| 5. | ቄስ ዳንኤል አርኬ እና የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ | 87190 | ቅጽ 15 | በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መስጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና የዳኘነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጐላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ብቻ ነው፡፡<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323(2) |
| 6 | እነ ወ/ሮ አለዊያ ዑመር እና አቶ ሐሺም ሁሴን | 90361 | ቅጽ 16 | በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር አይደለም ፡፡<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 1851 |

## 4.5የንብረት ህግ የይርጋ ደንቦች

በንብረት ህግ ውስጥ የተለያዩ አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተፈጠረበት ሰው ንብረቱ ይመለስልኝ ወይም ሁከቱ ይወገድልኝ ብሎ የሚያቀርበው ክስ ወይም አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ የተገደበ መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ 1149(2) ተገልጿል፡፡ ሌላው ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ እጅ ሆኖ ከንብረቱ የሚፈለገውን

ግብር ለ 15 (አስራ አምስት) ተከታታይ አመታት የገበረ ሰው የንብረቱ ባለቤት የሚሆንበትን አጋጣሚ የሚገልጸው ፍታብሀር ህግ ቁጥር 1168 ነው፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ህግ ቁጥር 1192 መሰረት ግዙፍነት ያለው የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለ ሀብት የሆነ ሰው ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ ወይም ሀብቱ መሆኑን ባለማወቅ አስር አመት ያልተገለገለበት እንደሆነ መብቱን በይርጋ ምክንያት ያጣል፡፡

በሌላ በኩል የንብረት ህግ ውስጥ ይርጋን በተመለከተ የሚነሳው አከራካሪ ነጥብ በፍራብሄር ህግ ቁጥር 1206 ድንጋጌ ስር አንድ ከሳሽ የቤቱ ባለሀብት በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ቤቱን ይዞበት የሚገኘውን ተከሳሽ በፍርድ ኃይል እንዲለቅ እንዲደረግለት የሚያቀርበው የመፋለም ክስ (petitory action) ይመለከታል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር 43600[44] ላይ በሰጠው ውሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል አይችልም የሚል የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የተለያዩ የህግ ምሁራን በዚሁ ጉዳይ ላይ የልዩነት ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡ ለአብነት ያህል ዶክተር ብሩክ ሀይሌ[45] በዚሁ ጉዳይ ላይ በጻፉት ጽሁፍ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር የተመለከተው የ 10 አመት የይርጋ ድንጋጌ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ ኃይል እንዲለቅ እንዲደረግለት ከሳሽ ለሚያቀርበው የመፋለም ክስ ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል በማለት ይከራከራሉ፡፡ እንደ ምክንያት የሚጠቅሱትም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1) መሰረት ግዴታዎች ከውል ባይመነጩም እንኳን የውል ደንቦች ተፈጻሚ ሊደረጉ ስለሚችሉ አንቀጽ 1845 የንብረት ክርክሮችንም በተመለከተ ተፈጻሚ መሆን ይችላል የሚል ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ ሰበር ሰሚ ችሎት በንብረት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 5</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንብረት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

[44] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 10፣ መዝገብ ቁጥር- 43600፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2003፣ ገጽ 225-229

[45] Biruk Haile, Period of Limitation Applicable to Claims over Immovable Property under the Ethiopian Law: Gateway to Hindsight Scrutiny of Legality of Nationalization of Immovables? Case Analysis Jimma University Journal of Law, Vol. 4 No. 1 (2012), page 183

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዳዊት መስፍን ና የመንግስት ቤቶች | 43600 | ቅጽ 10 | የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1677፣ 1845፣ 1206፣ 1188-1192 |
| 2. | ወ/ሮ ገብርኤሊ ኒካሊ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | 48048 | ቅጽ 10 | አንድን ንብረት በአደራ ለማስተዳደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ አለበት፡፡<br>ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የለም፡፡<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2)፣ 2779፣ 2989(1) |
| 3. | ሳሚኤል ታደሰ እና እጥፍ ወርቅ ሀ/ማርያም | 56011 | ቅጽ 11 | የኮንዶሚኒየም ቤት ባለሀብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት አመት ካለፈ በኋላ ነው፡፡<br>አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 21፣ 14(2) |
| 4 | አዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክና አዱኛ አበሉ | 53749 | ቅጽ 11 | በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መስሪያቤቱ ካወቀና እቃው የጉምሩክ ስነ ስርአት አጠናቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ካገር ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ውር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 368/95- አንቀጽ 15 |
| 5. | ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከበደ ወዳጆ | 59979 | ቅጽ 11 | በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(8) መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሳ በሁለት አመት ይርጋ አይታገድም፡፡ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1143 እና 2143 |
| 6. | አብዱ መሀመድ እና ዘበናይ ሀይሌ | 53328 | ቅጽ 11 | የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የይርጋ መርህ ንብረትን በመያዝ ወይም ባለ ይዞታ በመሆን የባለ ሀብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ ይለያል፡፡ ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1168 |
| 7. | አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም ና ወ/ሮ አስመረት መኮንን | 89148 | ቅጽ 16 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሠው ባለማቋረጥ ለ 15 ዓመታት ግብር በስሙ መክፈሉ ከተረጋገጠ የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን ይችላል፡፡ የፍ/ህ/ቁ 1168(1) |

## 4.6ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ የይርጋ ደንቦች

በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2143 መሰረት ከውል ውጭ ባለ ኃላፊነት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ቢሆንም ጉዳዩ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የወንጀሉ ይርጋ ዘመን ርዝመት ከሁለት ዓመት የበለጠ ከሆነ የካሳ ማቅረቢያው ጊዜ የወንጀሉን ይርጋ ጊዜ የሚተካ ይሆናል፡፡ ከላይ በተመለከተው ቁጥር መሰረት ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት ተፈጻሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ከውል ውጭ ሀላፊነትን በተመለከተ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ነገር ግን የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን ያካትታል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ሰበር ሰሚ ችሎት ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች (ትርጉሞች) ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ  እናያለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 6</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከውል ውጭ ባለ ሀላፊነት ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አረጋሽ ከበደ | 16062 | ቅጽ 3 | ከውል ውጭ ሀላፊነትን በተመለከተ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ |
| 2. | ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፕሬሽን እና ወ/ሮ ፊጤ ዓሊ | 34544 | ቅጽ 9 | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ስር የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን ያካትታል፡፡ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3. | አለምነው አበበ እና ህብረት ኢንሹራንስ | 58920 | ቅጽ 11 | ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት ተፈጻሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 (1) (2) |

## 4.7የንግድ ህግ የይርጋ ደንቦች

በንግድ ህጎቻችን ውስጥ የተለያዩ አይነት የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ በንግድ ህጉ[46] አንቀጽ 807(2) መሰረት ተላላፊ ሰነዶችን በተመለከተ የሀዋላ ወረቀትን ለክፍያ እሽ ብሎ በተቀበለ ባለ እዳ ላይ የሚቀርቡ ክሶች የመክፈያ ቀን አልፎ በሶስት አመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ይታገዳሉ፡፡ ሌላው ቼክን የተመለከተ የይርጋ ደንብ በዚሁ ህግ ቁጥር 881(1) የተገለጸ ሲሆን አምጭው የቸኩ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኂላ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ካልመሰረተ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በዚሁ ህግ ቁጥር 855 መሰረት ቼክ ለክፍያ የሚቀርበው ከተጻፈበት ቀን አንስቶ በሚከተሉት ስድስት ወራት ውስጥ ነው፡፡ ቼክ አምጭው በከፋዩ ላይ የሚያቀርበው ክስ የይርጋ ዘመን ሶስት አመት አንደሆነ በንግድ ህጉ ቁጥር 881(3) ተመልክቷል፡፡ የሀዋላ ወረቀት አምጭ በጀርባ ፈራሚወችና በአውጭው ላይ የሚያቀርበው ክስ በአንድ አመት ይርጋ እንዲሁም ፈራሚወች እርስ በርሳቸውና በአውጭው ላይ የሚያቀርቡት ክስ በ ስድስት ወር ይርጋ እንደሚታገድ በቁጥር 817(2) እና (3) ተመልክቷል፡፡ ሌላው በየብስና በአየር ማመላለስ አገልግሎት ውሎች ውስጥ በመንገደኛው ላይ ለሚደርሰው የአካል ጉዳት እንደዚሁም ለእቃ ብልሽትና ለንዝ መጥፋት በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካልቀረበ አንዡ ጉዳቱን ለመካስ እንደማይገደድ በንግድ ህጉ ቁጥር 603 እና 642 ተደንግጓል፡፡ በዚሁ ህግ ቁጥር 674 ላይ ደግሞ በመድን ውል ምክንያት የሚቀርብ ክስ ጉዳቱ ከተደረገበት ወይም በጉዳቱ ጥቅም ያላቸው ሰወች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ አንመለከታለን፡፡

[46] የኢትዮጵያ ንግድ ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 52/1952፣ አንቀጽ 807

## <u>ሰንጠረዥ 7</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | 42309 | ቅጽ 9 | ኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሟል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሀሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 674(1)(2) |
| 2. | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | 46778 | ቅጽ 10 | የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል፡፡ የንግድ ህግ ቁ. 674(1)፣ 754(1) |
| 3. | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ቃድሮ ኑሬ | 56010 | ቅጽ 12 | ገንዘብ አበዳሪ የሆነ ባንክ ግዴታውን ለመፈጸም ያልቻለን አበዳሪ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኋላ ቀሪውን እዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይችላል፡፡ፍ/ብ/ህ/ ቁ. 1846 |
| 4. | ሀጅ መሀመድ እና ፍጹም ግርማ | 24435 | ቅጽ 12 | ቸክ በመፈረማቸው ምክንያት በሚገደዱ ሰወች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው ቸኩ ከተጻፈበት ቀን አንስቶ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 855 |
| 5 | አቶ ሐሠን መሀመድ እና ማጅ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | 94278 | ቅጽ 17 | ክሱ የቀረበው በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን መሠረት አድርጐ ሲሆን የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ወይም ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ምክንያት አይኖርም፡፡<br>የንግድ ሕግ ቁ. 218(1)፣ 541(1) የፍ/ሕ/ቁ/ 1835፣1845 |

## 4.8የቤተሰብ ህግ የይርጋ ደንቦች

በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ[47] ውስጥ የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች አሉ፡፡ በዚሁ ህጉ አንቀጽ 69 መሰረት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ ባል ወይም ሚስት ፈቃድ ሳይሰጥ/ሳትሰጥ ያለ አንዱ ወገን ስምምነት የተደረገ የሽያጭ ውል ስምምነቱን ባልሰጠው ወገን ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ውሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ውሉ ከተፈጸመ በ ሁለት  አመት ውስጥ ካለቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍታብሄር ህግ ቁጥር 826(1) እና 1846 በሰጠው ትርጉም መሰረት ጋብቻ በባል ወይም በሚስት (በአንዱ ወገን) ሞት ምክንያት ከፈረሰ በኋላ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት እለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ አይደለም፡፡[48] ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት መጠየቅ ያለበት በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 ላይ በተቀመጠው ይርጋ ደንብ መሰረት በ አስር አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡[49]

ሰበር ሰሚ ችሎት ቤተሰብ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ ተመላክተዋል፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 8</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቤተሰብ ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና እነ አቶ አባተ ጫኔ | 17937 | ቅጽ 4 | ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል<br>ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ |

[47] የኢፌዴሪ የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 213/92፣ አንቀጽ 69
[48] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ ቅጽ 11፣ መዝገብ ቁጥር- 59539፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2004፣ ገጽ 199፡፡
[49] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔወች፣ ቅጽ 4፣ መዝገብ ቁጥር-17937፣ የኢፌዲሪ ጠ/ፍ/ቤት የጥናትና የህግ ድጋፍ መምሪያ፣ 2001፣ ገጽ 82፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. | አቶ ዮሀንስ ጡእማይ እና ወ/ሮ ምህረት ገብሩ | 51295 | ቅጽ 10 | በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ ያለስምምነት የተደረገ የሽያጭ ውል ስምምነቱን ባልሰጠው ወገን ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ውሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ውሉ ከተፈጸመ በ ሁለት አመት ውስጥ ካለቀረበ በይርጋ ይታገዳል። የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69 |
| 3. | አቶ ስዩም እና ወ/ሮ አምሳለ | 59539 | ቅጽ 11 | ጋብቻ በአንዱ ወገን ሞት ምክንያት ከፈረሰ በኋላ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት እለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ አይደለም። የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 826(1)፣ 1846 |

## 4.9የወንጀል ህግ የይርጋ ደንቦች

በወንጀል ህግ ይርጋ የክስ ይርጋ እና የቅጣት ይርጋ በሚል በሁለት ይከፈላል።[50] የክስ ይርጋን በተመለከተ እንደ ወንጀሉ ክብደት የይርጋው ጊዜ ይለያያል። ዐቃቤ-ሕግም ሆነ የግል ተበዳይ ወንጀል ፈጽሟል በተባለው ሰው ላይ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝር አሰራሩ በኢፌዴሪ ወንጀለኛ ህግ[51] አንቀጾች 216-222 ተገልጿል። በዚህ ህግ 217 እንደተገለፀው ከፍተኛውን ቅጣት ማለትም የሞት ፍርድ ወይም የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራትን ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ከተባሉ ከ25 ዓመት በኋላ ክስ አይቀርብባቸውም። እንደ ወንጀሎቹ ክብደት፣ ከአምስት እስከ 20 ዓመት የይርጋ ዘመን የሚታገዱ የተለያዩ ወንጀሎች በዚህ አንቀጽ ውሰጥ ተካተዋል። በሌላ በኩል ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በእስራት ሊያስቀጡ ወይም በገንዘብ መቀጫ ብቻ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን ሶስት ዓመት ነው። በወንጀል ህጉ አንቀጽ 218 እንደተገለጸው ልዩ የይርጋ ዘመን አለ። ይኸውም በግል ተበዳዮች አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ነው። የዚህ ዓይነት ወንጀል የይርጋ ጊዜ ሁለት ዓመት ነው።

ሁለተኛው አይነት የወንጀል ህግ ይርጋ ደንብ የቅጣት ይርጋ ሲሆን ከቅጣት አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ነው። አንድ ሰው ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ቅጣቱ ሳይፈፀም ቢቀር በሕግ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ ቅጣቱን የማስፈፀም መብት እንደሚቀር የወንጀለኛ

50 ጥላሁን ተሾመ፣ የግርጌ ማስታወሻ 2፣ ገጽ 184

51 የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 414/96፣ 1997

መቅጫ ህግ ቁጥር 223 ይናገራል፡፡እንደ ወንጀሉ ክብደትና ቀላልነት የቅጣት ይርጋ በሰላሳ ፣ በሃያ፣ በአስርና በአምስት ዓመት ሊወሰን እንደሚችል የዚህ ህግ ቁጥር 224(1) ዘርዝሮ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች በተመለከተ የሰጣቸውን ውሳኔወች ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ አንመለከታለን፡፡

**<u>ሰንጠረዥ 9</u>. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀል ህግ ውስጥ ስለሚገኙት የይርጋ ደንቦች የሰጣቸው የህግ ትርጉሞች**

| ተ.ቁ | የባለጉዳዮቹ ስም | የሰበር መዝገብ ቁጥር | ውሳኔው የሚገኝበት ቅጽ ቁጥር | ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው የይርጋ ህግ ትርጉም ማጠቃለያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌዴራል አቃቤ ህግ | 45572 | ቅጽ 11 | በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ሊይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን አያግደውም፡፡ |
| 2. | ሀይላይ ተክሉና የመቀሌ ከተማ አቃቤ ህግ | 77097 | ቅጽ 14 | በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን ያቋርጣል፡፡<br>የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 221፣ 106(1)፣ 420 (2)፣ 271(1)፣ 219(2) |
| 3 | እነ አቶ አዳሙ ዘለቀ(3 ሰዎች) እና የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ | 95875 | ቅጽ 16 | አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ በሌለበት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቀርቦ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስነሳት ሳይሆን በዋናው ጉዳይ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ከጠየቀ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ብሎ ቢያመለክት በፊት የጠየቀው ይግባኝ በህጉ ላይ የተቀመጠውን የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ያቋርጠዋል፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.198 |

# 5 ማጠቃለያ

የይርጋ ደንብ ሁለት አይነት መልክ ሲኖረው የመጀመሪያው ግዴታ አስቀሪ የይርጋ ደንብ ሲሆን ሁለተኛው አይነት የይርጋ ደንብ ደግሞ ያልነበረ መብት የሚያስገኝ የይርጋ ደንብ ነው፡፡ የይርጋ ደንብ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሕግ ተቀባይነት ያለው ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ተከራካሪዎች፣ ዐቃቤ-ሕግ፣ ፍርድ ቤቶች፣ ጠበቆች እና የህግ ባለሞያዎች በጥንቃቄ ሊያጤኑት የሚገባ ለክርክር የቀረበን ጉዳይ እጣ ፈንታ ሊወስን የሚችል ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ የይርጋ ደንብ የራሱ የፖሊሲ መሰረት ያለው ነው፡፡ አንድ የመብት ጥያቄ በህግ ፊት ተቀባይነት ቢኖረውም እንኳን ሊቀርብ በሚችልበት ጊዜ ላይ ገደብ ማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ህጉ ዳተኛውን ባለገንዘብም ቢሆን ማስጠንቀቅ ያስፈልገዋል፡፡ የይርጋ ደንብ የሚፈጥረው አጠቃላይ ዋስትና ከጉዳቱ አንጻር ሲታይ ሚዛን ይደፋል፡፡

የይርጋ ደንብን አስመልክቶ በተለያዩ የኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ የተካተቱት ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያመላክቱት ክስ ለማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ክስ ለማቅረብ ወይም መብት ለመጠየቅ እንዲቻል በሕግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብም እንደጉዳዩ ክብደት፣ ባሕሪና ሁኔታ የተለያየ ሲሆን ለሁሉም ጉዳዮች የተቀመጠ ተመሣሣይ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የለም፡፡ በመሆኑም ሕግ አውጪው እንደ ጉዳዩ ዓይነት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስን ለማቅረብ  ወይም ያልነበረን መብት ለማግኘት  የሚያስችሉ የጊዜ ገደቦችን በሕጎች ውስጥ እንዲካተት አድርጓል፡፡

በወንጀል ጉዳይ ላይ ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችሉት ተከሳሽ፣ ዐቃቤ-ሕግና ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ የፍትሐብሔር ፍሬ ጉዳይ የይርጋ ደንቦችን በተመለከተ ዳኞች በተከራካሪወች ካልተነሳ በቀር በገዛ ሥልጣናቸው የይርጋውን ደንብ በመቃወሚያነት ለመጥቀስ አይችሉም፡፡ ነገር ግን በስነ-ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረ የይርጋ ጊዜን በማሳለፍ የሚቀርብ ጥያቄን ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ ይችላል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተከራካሪ (ተከሳሽ) ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር የሚችለው ለቀረበው ክስ የመከላከያ መልስ በጽሑፍ ሲሰጥ ነው፡፡ እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽ ለፍርድ ቤቱ ማንነቱን ካስመዘገበና ክስ ከተነበበለት በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክስና መከራከሪያ ከመቅረቡና ማስረጃም ከመሠማቱ በፊት ይርጋን በመቃወሚያነት አንስቶ ለመከራከር  ይችላል፡፡

ጥቂት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ክስ የማቅረቢያ ወይም መብት የመጠየቂያ ጊዜ ገደብ እንደሌለና ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ያለምንም የጊዜ ገደብ

በማንኛውም ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚቻልባቸው ጉዳዮች እንዳሉ በዚህ ጽሁፍ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ባካሄደው ጥናት የኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ድንጋጌወችን በተመለከተ በፍታብሄር ስነ-ስርአት ህግ፤ በውል ህግ፣ በውርስ ህግ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ፣ ከውል ውጭ ሀላፊነት፣ በንግድ ህግ፣ በቤተሰብ ህግ፣ በንብረት ህግ እና በወንጀል ህግ ዙሪያ ከቅጽ 1 (አንድ) እስከ ቅጽ 17 (አስራ ሰባት) ድረስ 70 (ሰባ) ያህል የህግ ትርጉሞችን ሰጥቷል፡፡ ይህ ጽሁፍም ውሳኔዎቹን በመለየትና አንዳንድ የህግ ምሁራን በውሳኔወቹ ላይ ያነሷቸውን አስተያየቶች በመተንተን ለአንባቢያን ምቹ በሆነ መልኩ አቅርቧል፡፡